# ይድረስ ለሠርካለም ዘቃሊቲ

ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ

ዶክተሮች ተጠርተው
ሊያዋልዱሽ ብለው
ነርሶች ተደርድረው
ሊያቋቁሙሽ አብረው
ሆስፒታል ክሊኒክ
ሲናፍቁሽ ከርመው
ከቃሊቲ ታዛ
ወረድሽ ከዘብጥያው
ለካስ ጉዳይ ኖሮሽ
ተመረጠ ወህኒው

ታማኝስ እንዳንቺ
ያገባ ወጥቶ-አደር
ካመሸበት ውሎ
ካደረበት ማደር
ቤትም ሆነ ወህኒ
እንዲህ ነው አብሮ መኖር !

ማርያም ማረችሽን
ከቤተሰብ ሲያምርሽ
የታደልሽ አንቺ ነሽ
ከሕዝብ ተሸለምሽ
በታዛ መወለድ
በጌታችን ቀንተሽ
ልትወልጂ መዶለት
ከዘብጥያ ወርደሽ?

ልዩ መሆንሽን
በቃ ተረድተናል
ከጌታችን በላይ
ምሳሌን ጠልተናል

መች የሰው ምርቃት
የእግዜር በረከት ነው
በራሱ ልደት ቀን
የታቀፈ ማነው?

አንቺንስ ይበልሽ
ወጥቶ-አደሩን ጭምር
ታዲያ ሕፃኑን ምነው
ፍቅር በልክ ሲያምር
የልጅ ጡር ክፉ ነው
በሰማይም በምድር
መወለዱስ በጀ
ክርስትናስ ይቅር
ወዳጅ ዘመድ ይኑር
በሰፊው ይዘከር

ልደት በዓልና
ክርስትናም ጭምር
ያለሥም መች ሆኖ
ሁሉን ለመዘከር
ምኒልክ ሳተናው
አስኳልም ምርጫ ነው
ሥሙን ከከተብሽው
ሠርካለሜ ማነው?
ታዋቂውን ታጋች
ጨቅላውን ናፈቅነው
እመጫት እሥረኞች
እኛስ ተላመድነው !

*************************

© ድሚልኝ ብህሬ-ዘአዲሱ ገበያ
ሰኔ 1998
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
June 2006